# እግርን ቀይዶ ዝላይ አይቻልም

የኢትዮጵያ ሀገር ወዳድ ዜጎች ወያኔን አውድመው፣ ሀገራቸውን ሊረከቡና ባለቤት ሊሆኑ ምኞታቸው ነው። አውድመው፣ ጠራርገው፣ ወደ ትቢያ ጉድጓድ ጥለው ነው መሰረታዊው ቃል ወይም ግንዛቤ። ይህም የሚያመለክተው በቅድሚያ በሰበብ አስባቡ በወያኔ ላይ ቁርጠኛ አቋም አለመያዝ ጥፋት መሆኑን ይጠቁማል። ከወያኔ ጋር በሰበብ አስባቡ ለመተቃቀፍ መጣር ሀገርን ጎጂ መሆኑን ያስያል። ከመሞዳሞድ አልፎ ከወያኔ ጋር መወዳጀት፤ በወያኔ ላይ ማዕቀብ አለማድረግ፤ ሀገርን መቀራመት፤ በዝርፊያው ድርሻ መሻትና በግርግሩም ሀገርን ለመገነጣጠል መነሳት ደግሞ ከወንጀልም ወንጀል መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያመለክታል።

እግርን ቀይዶና አስሮ ዝላይ የሚቻል እንደማይሆነው ሁሉ በወያኔ ላይ ቁርጠኛ አቋምን ይዞ በተግባራዊ ትግል ሳይሰማሩ ደግሞ የወያኔን ውድቀት መመኘቱ ጅልነት ቢባል ስህተት አይሆንም። ወያኔን አምርሮ ለመታገል ጽኑ አቋምና ጥረት ካለ የፖለቲካውን መድረክ የሚያደፈርሱትን፤ ፖለቲካና ንግድ ተወራራሽ የሆነባቸውን፤ በትግል ሽፋን ውዥንብር የሚነዙትን ሁሉ ጥግ ማስያዝ ማግለል ይቻላል። ይህ ሳይደረግ ህብረትንም፤ ትግልንም፤ ድልንም መመኘቱ ሞኝነት ይሆናል። የአያሌ ችግሮች መንስኤ ወይም መነሻ የራሳችን ውስጣዊ ድክመት መሆኑ መታወቅም አለበት። አሁንም ቢሆን የተቃዋሚው ጐራ አድርባዮችና ከፋፋዮች የሚርመሰመሱበት መሆኑ ግልጽ ነው። ራሳቸውን ህጋዊ ተቃዋሚ ያሉት እንኳን ለመሰባሰብና ለመተባበር አቅቷቸው አ። በፖለቲካው መስክ ራሳቸውን ኢንጂነር ባዮቹ የገነቡት የእምቧይ ካብ እንጂ ሌላ አልሆነም። አንዳንዶቹ ከጠባብነታቸውና ወያኔነታቸው አልላቀቅ ብለው ለህብረትም ለትግልም እንቅፋት በመሆን እየተሰነጣጠቁ ናቸው። ራሱን አረና ትግራይ የሚለውን ቡድን ያጢኗል። ታጋይ ድርጅቶችን ከፋፍለው ለወያኔ የጠቀሙትም ዕድገት ሳይሆን ውድቀት ዕጣቸው ሆኖ ሲያፈጥባቸው በተነቃበትና በጠነዛው መንገዳቸው/ዘዴያቸው የታጋዩን ጎራ ዳግም ሊሰርጉ እየጣሩ ናቸው። ማን ድርጅቶችን ሲከፋፍል ባጀ? የትኛው ድርጅቶ ነው ሊሎችን ለማዳከም የተቋቋመ? ማን ደግሞ ደጋግሞ የህብረት ጥረትን ሲያበላሽ ቆየ? ማንስ ድርጅት ነው ለባዕዳን ያደረ? ለነዚህና መሰል ጥያቄዎች ምላሽ መስጠቱ ጸረ ወያኔውን ትግል ፈር ያስይዘዋል።

ትግል ቧልት ወይም በአቦ ሰጡኝ የሚካሂድ ሳይሆን ስልትን፤ ጥንቃቄን፤ ሙያተኛነትን ጠያቂ ነው። የድርጅት ምስጢር የባቂላ ወፍጮ መሆን የለበትም--በህይወት መጠበቅ ያለበትም ነው። የድርጅትን ምስጢር አሳልፈን አንሰጥም ብለው ራሳቸውን የሰዉ የኢሕአፓ አባላትና መሪዎችን ያስታውሷል። ድርጅት ክፍትና ዝርክርክ ከሆነ ጠላት በቀላሉ ምስጢሩን ያውቅበታል፤ ጠላት በቀላሉ ሰርጎትም ይገባል--በትግልና ሕይወት ላይ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ቀላል አይሆንም። ኢሕአፓ ለምሳሌ ሲጀምር የነበረውን አወቃቀር በርካታ ጊዜ የቀየረ ሲሆን ወያኔ ለስልጣን ከበቃም በኋላ ኢሕአፓን ሊያጠቃ ሲጥር የድርጅት ይዘቱንና የመዋቅሩን ይዘት ቀይሯል። አንጃዎችና ከሃዲዎች ሲፈሉም የነበረውን የሀገር ቤት መዋቅር ሳይታክት ቀያይሯል። ይህ ራስን ከጥቃት መከላከል ነው። ራስንም ከአፍራሾችና መዥገሮች መከላከልም የትግሉ አካል መሆን አለበት። ማለትም ውስጣዊ ድክመትን ማስወገድ ካልተቻለ የውጩን ወያኔ ማቸነፍ ከባድ ይሆናልና ነው። ድርጅትን ጨጎጊቶችንም ሆነ ጎታቾችን አጽድቶ፤ የትግልና የፖለቲካ መድረኩንም ከነጋዴዎች አላቆ መገኘቱ ለትግሉ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ይህም ጉዳይ ድርጅትን ብቻ ሳይሆንም ሕዝብንም የሚመለከት ነው።

ሕዝብ የታጋይና ጀግና ትርጉም ጠፍቶት አላፊ አግዳሚውን አፈ ጮሌና የመድረክ ተዋኒ ከያኒ መሪዬ ብሎ ካቀፈ ትግሉን ይጎዳል። ወያኔውን ስዬ አብርሃን መሪ ሊሉ የቃጡትንና ግለሰቡን የሕዝብ ትግል መሪ ማለት ስህተት ነው ብለው የተቃወሙትንም ሊያወግዙ የጣሩትን የምንረሳ አይሆንም። ደግሞ ደጋግሞ ተመክሮ ያሳየን ሆኖ ሳለ አሸፈረን አንማርም ማለቱ ትግላችንን ደግሞ ደጋግሞ በ አፍጢሙ ደፍቶታል። ራሳቸውን ለመስዋዕትነት ያቀረቡ ጀግኖች ተረስተው በወር (ያውም በተዘጋጀ) የእስር ቆይታ ማንዴላ ሲባሉ የነበሩ ቡከኖችንም አይተናል። ዛሬ የፖለቲካው ጉዳይ ተንከባሎ እነማን ጋ እንደደረሰ ምስጢር አይደለም። ቆራጥነት ያነሰውና ብቃት አልባ በሆኑ የሚመራ ደግሞ ይደናበር እንደሆነ እንጂ ወደ ድል ማንንም አያደርስም። የነጋዴዎችና አስመሳይ ታጋዮች ሰለባ ሆኖ ለመቅረት ያልፈለገ ህዝብ ብቃትና ጀግንነትን የቀልድ ጉዳይ አያደርግም። ነጋ ጠባ በቀበሮዎች አይታለልም። ታጋይ ልጆቹን ያወድሳል ይደግፋል እንጂ ታፔላ ለለጠፈ ምሁር በሉኝ ባይ ጆሮውንም ልቡንም አይሰጥም። አንዲዬ መታለል ይረዳናል፤ ነጋ ጠባ ግን መነዳት መታለል የሞኝ ፈሊጥ ያሰኛል። ስለዚህም ጠንቀቅን አለማራቅ ተገቢ ይሆናል ማለት ነው።

ወይኔ በሰሞኑ የደም ተመክሮ አይደገምም በሚል በኢሕአፓ ላይ ክሱን እየደረደረ ነው። ለአህያ ሃውልት የሰራው ወያኔ ቧልተኛም ነውና ለጸረ ኢሕአፓ አንጃዎች ሀውልት ልስራ ብሎ ሰበር ሰካንም ከዚሁ አያይዞ ጀምሯል። ስጋቱ የሕዝብን ጎራ የሚያስደስት ሲሆን በወያኔ ቅስቀሳ ሊወናበዱ የሚፈቅዱ ካሉ ደግሞ ዕዳው የነሱው ነው። ብዙ ፍንጮች ወያኔ ሀገሪቷን በሰሜን ለጦርነት ሊዳርጋት ነው በሚል ይጠቁማሉ። ሆነም አልሆነም ግን ህዝብ ለወያኔ ተወናብዶ 120 ሺዎች ከዚህ ቀደም ለወያኔ ጭዳ እንደሆኑት ራሱን ለሞት ማስበላት የለበትም። ከ ትላንት ጀምሮ የሕዝብ መስዋዕትነት ለወያኔ ሳይሆን ለሀገሩ፤ ለሀገር አድን ትግሉ ድል ብቻ መሆን እንዳለበት ተደጋግሞ የተገለጠ ነው። በሰላማዊ ትግል ሽፋን ጸረ ወያኔ ትግልን ሊያሽመደምዱ የሚጥሩት በአብላጫው ለወያኔ ያደሩ መሆናቸው ግልጽ ቢሆንም ሰላማዊ ትግል (በሚገባው መንገድ ከተካሄደ) የሁለ ገቡ ትግል አካል መሆኑ አይካድም። ስንቶቹ የሰላማዊ ትግል አባወራዎች ለሙብት ብለው ሲሰለፉ፤ የታሰሩት ይፈቱ ብለው ሻማ ሲያበሩ አይተናል ከወሬው ባሻገር? ከዚህ በከፋ መንገዱ አይደል ደብዛቸው የጠፋን፤ ከሱዳን ከኬንያ ወዘተ ታግተው ለወያኔ የተሰጡትን፤ ታስረው ሲማቅቁ ዓመታት ያሳለፉትን "የእኛ አይደሉም" ብለው ስማቸውን ሳይጠቅሱ እንኳን የቀሩት? ዲሞክራሲ ለእኛ ሌላው ግን ይረገጥ ፖለቲካ መስመርን ይዞ ሀገርን ከጥፋት ለማዳን መቃጣት ዘበት ነው። ግማሽ ሀገር ወይም ግማሽ ሙብት የሚባል ነገር የለም። ለሀገሩ ባዳ መሆንንም እጁን አጣጥፎ የሚቀበል ይኖራል ብሎም መጠበቅ-መገመት ስህተት ይሆናል።

ስለሆነም የህገር አድን ትግሉ በቅድሚያ የእስከዛሬ ድክመትን ማወቅና ለማስወገድ መነሳትን ይጠይቃል። ደማችን እየፈሰሰ፤ ሕይወት እየተገበረ፤ ማጎሪያው ሞልቶ፤ ስየሉ መረን ለቆ ባለበት ለምን ትግሉ ድልን መቀዳጀት አቃተው። ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር ነውና መፍትሔው ወደ ራስችን መላላትና ድክመት ትኩረትን ማዞሩና ጥንካሬን መሻቱ አግባብ ያለው ይሆናል። ስህተትን ለመድገም ግን እሽቅድምድሙን ማንንም አሸናፊ ሳያደርግ ሁሉንም በአፍጢሙ የሚደፋ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። የመሪ ድርጅት ጽንሰ ሀሳብ ድክመቱ ከዚህ ቀደምም ተጠቁሟል። ከእኛ ውጪ ሌላ ድርጅት የለም የሚለውም ዕብሪት ትግልን የሚጎዳ መሆኑን የአወቅነው ጉዳይ ነው። ድርጅት ትህትናና ከጉራ መራቅን መርሁ ሊያደርግ ይገባል። ዕይታን ሰፋ አድርጎ፤ ከተመክሮ ተምሮ፤ ይበልጥ ለመማር ዝግጁም ሆኖ በገቢር በትግሉ መሰማራት ቀና ነው። ድርጅት ራሱንም ሲገመግም ለራሱ ሊዋሽ አይጠበቅም። በተፃራሪው እንዲያውም ራሱን አብጠርጥሮ እንዲገመግም ይጠበቃል። መለስ ብለን ለመሆኑ ስንቱ የተቃዋሚ ድርጅት ነው ጠቅላላ ጉባኤ አድርጎ አባላቱን ለግምገማ ሰብስቦ፤ አመራሩን በአባላቱ የሚያስመርጥ? አመራሩ ተሰብስቦ አይደል ሁሉንም ወስኖ ለአባላት የሚያወርደው? አንድ

ግለሰብስ እንዳፈተተው የሚወስንበት ድርጅት የለም ማለት ይቻላል? ወያኔን ለማሸነፍ ይህንንና ሌሎችንም ድክመቶችን ማስወገድ ያስፈልጋል። ነብርን በአርጩሜ ለመሸኘት መቃጣቱ ማቆም ማከተም አለበት። ጉልበት ያለውን አገዛዝ ለማቸነፍ ጉልበት ያለው ተቃዋሚ--ማለትም ሕዝብን አደራጅቶና አቅፎ የሚታገል-የሚያታግል-- ያስፈልጋል። የወረቀት ነብር አማጽያንን ይዞ ፈቅ ማለት አይቻልም። በኤርትራ ከተሙ፤ ሰለጠኑ ወይም ታጠቁ የተብሉት ሁሉ ምን ጠቀሙን? ምንም ነው መልሱ። የሚዳሰስ የሚታይ አቅም ይዘው ሊገኙ አልቻሉምና ተጨፈኑ እናሞኛችሁ "ወታደራዊ መግለጫቸው"--በአብዛኛው ላም ባልዋለበት የኩበት ወሬ-- ማንንም ሊያሳምን አልቻለም። አምነው የሂዱትም በመጡበት ፍጥነት ሸሽተዋል ወይም ሊያመልጡ ሲጥሩ ለሰው በላዎቹ ሰለባ ሆነዋል።

የባእዳንም ሰልፍ አልቀይር ካለ 23 ዓመታት ጨፍልቀውን ተጉዘውብን አሁንም ያድኑናል ብሎ መመኘቱ የራሳችንን ሞኝነትና የንቃት ጉድለት የሚያጋልጥ ነው። ባእዳን የሚያስቀድሙት የየራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም ነውና ይህንን የሚያስጠብቅላቸው ሎሌያቸው ወያኔ እስከሆነ ድረስ በሁሉም መስክ--በውሸቱም ጭምር--ያጅቡታል። ይረዱታል፣ ይታደጉታል። ይህን ሁኔታ ለመለወጥ የሚያስፈልገው ምለላ ሳይሆን ሁኔታውን በትግል መለወጥ ነው። ማለትም ወያኔን ባመረረ ትግል መወጠርና ባእዳን ለጥቅማቸው ሲሉ እንዲከዱት ማስገደድ ማለት ነው። አሜሪካ ከቪየትናምም ሆነ ከሶማሊያም ሆን ከሊባኖን እንዲወጣ የተደረገው በነበረው ጉዳት፣ በደረሰበት ትግል ነው። አሜሪካ የሚያፈቅራቸውን አምባገነኖችን (የኢራኑ ሻህ፤ ሞቡቱ፤ ሙባረክ፤ ወዘተ) እንዲተው የተደረገው በሀይል እንጂ በልምምጥ አልነበረም። ትምህርቱ ግልጽ ነው--ባእድን ወያኔን መደገፍ ዋጋው ከፍተኛ ነው ብለው እጃቸውን እንዲሰበስቡ ማድረግ ያሻል ማለት ነው። ይህን ስንል ስለምዕራቦቹ የተባለው ሁሉ ቻይናንም፤ ህንድንም፤ አረቦቹንም የሚመለከት ነው ።

ቀንበራችንን ከጫንቃችን እናንሳ። በትግል ስም መዘረፍና ማላገጫ መሆናችንም ያክትም። ውስጣችንን እናጽዳና የሀገር አድኑን ጎራ እናጠናክረው። ከመዝለላችን በፊት ለውድቀት የሚዳርገንንና የቀየድንን ስህተት፤ ድክመት ሁሉ እናስወግድ። ስል ትግል ማውራቱን ቀንሰን በትግል መሰማራቱን እናብዛ ።